Washington State Department of
CHILDREN, YOUTH & FAMILIES

# ለምርመራ የተሰጠ ማሳወቂያ እና ፈቃድ

**ዓላማ፡-** ምርመራ እንዲከናወን ሃሳብ የቀረበ እንደሆነ ለወላጅ(ጆች) በጽሁፍ ማሳወቂያ ለመስጠት እና ምርራውን ለማድረግ ከወላጅ ፈቃድ ለማግኘት።

| **የልጅ ሥም** | **የትውልድ ቀን** | **የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ** |
|---|---|---|
| | | |

**ማሳወቂያው የተሰጠበት ምክንያት**
ESIT የምርመራ(የመለየት) ተግባራትን ከማከናወኑ በፊት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ እንዲሰጥዎ ይገደዳል። ለእነዚህ ተግባራት ከዚህ በታች በሚያሰፍሩት ፊርማዎ አማካኝነት በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ የጽሁፍ ፈቃድ እንዲሰጡ ያስፈልጋል። የምርመራ ዓላማ ልጅዎ በ ESIT ፕሮግራም ውስጥ ግምገማ/ምዘና ያስፈልገው እንደሆነ ለመወሰን ነው። ይህ ያንን ማሳወቂያ በተመለከተ ለእርስዎ የተሰጠ መግለጫ ነው።

*"ፈቃድ" ሰጥተዋል ማለት፦ ( (1)ፈቃድዎ ከተጠየቀባቸው ተግባራት ጋር የተያያዙ ማናቸውንም መረጃዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ (ይህንን ለማድረግ የማይቻል መሆኑ ግልጽ ካልሆነ በስተቀር) ወይም እንደ አግባብነቱ የምልክት ቋንቋን፣ ብሬልን፣ ወይም የቃላት ተግባቦትን ጨምሮ በሌላ የተግባቦት መንገድ ሙሉ በሙሉ ማግኘትዎን። (2)ፈቃድዎ ስለተጠየቀባቸው፣ ተግባራት ተረድተው እነዚህን ለማከናወን በጽሁፍ ፈቃድ መስጠትዎን (3) ፈቃዱ የሚከናወኑትን ተግባራት እና ለሌሎች ሰዎች የሚሰጡትን ማህደሮች (ካሉ) ለማን እንደሚሰጡ ጨምሮ ይዘረዝራል፤ እና (4) ፈቃድዎን የሰጡሁት በፈቃደኝነት መሆኑን እና በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ በማሳወቅ ሊያነሱት እንደምችሉ መረዳትዎን። ፈቃድዎን ካነሱ፣ ወደ ኋላ የሚሰራ አይሆንም* (ማለትም፣ ፈቃዱ ከመነሳቱ በፊት ለተወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች አያገለግልም)።

**እንዲወሰድ የቀረበ እርምጃ**
ልጅዎ ከዚህ በታች ካሉት የዕድገት ክልሎች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆነው የዕድገት ክልል ምርመራ ይደለታል ፡- የአእምሮ፣ የአጢቃላይ እንቅስቃሴ፣ የሰውነት ክፍሎች እንቅስቃሴ፣ ተግባቦት፣ ማህበራዊ-የስሜት፣ ራስን የማላመድ፣ የዕይታ፣ እና የመስማት። የምርመራ ውጤቶቹ በ ESIT ፕሮግራም ውስጥ ግምገማ/ምዘና መካሄድ ያስፈልገው እንደሆነ ለመወሰን ጥቅም ላይ ይውላሉ። ነገር ግን በምርመራ ሂደቱ በማንኛውም ጊዜ ላይ ግምገማ እንዲከናወን ከጠየቁ ወይም ፈቃድዎን ከሰጡ፣ ልጅዎ የአካል ጉዳት ይኖርበት እንደሆነ ባይጠረጠርም እንኳን ግምገማው ይከናወናል። በምርመራ ሂደት ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም መረጃዎች እና የምርመራ ውጤቶች በሚስጥር ይያዛሉ።

**መግለጫ**
ምርመራው የሚከናወንበት መንገድ በልጅዎ ፍላጎት መሰረት ይለያያል። የሕክምና/የዕድገት ማህደሮችን መመልከትን፣ ወላጆችን ማነጋገር፣ በልጁ ላይ የሚደረግን ምልከታ፣ እና/ወይም መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የዕድገት ምርመራ ሰነዶችን ማስተዳደርን ሊያካትት ይችላል። ምርመራውን የሚያከናውነው ሰው ስለእነዚህ ዘዴዎች እና ውጤቶች ከእርስዎ ጋር ይነጋገራል።

**የጊዜ ሠሌዳዎች**
ልጅዎ ግምገማ/ምዘና ያስፈልገዋል የሚል ውሳኔ ከተሰጠ፣ ልጅዎ ወደ ESIT ፕሮግራም ከተመራበት ቀን አንስቶ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ ግምገማው/ምዘናውን እና በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ዝግጅት መጠናቀቅ አለበት። ቤተሰብዎ ከ45 ቀናቱ በላይ ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልግ ከሆነ፣ ለቤተሰብ መረጃ አስተባባሪዎ መንገርዎ አስፈላጊ ነው።

*ልጅዎ ወደ ESIT ፕሮግራም የተመራበት ቀን፡፡* ______

**ማረጋገጫ እና የፈቃድ መግለጫ**
ከዚህ ማሳወቂያ ጋር በ*IDEA* ክፍል ሐ (የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ፣ *የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ(IDEA) ክፍል ሐ የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎችን [የወላጅ መብት]) ያሉኝ መብቶች እና የሥነስርዓት ጥበቃዎች ቅጂ ደርሶኛል።*

______________________________________
*የወላጅ ሥም የመጀመሪያ ፊደላት*

እነዚህ መብቶች ተብራርተውልኝ እኔም ተረድቻቸዋለሁ። ፈቃዴ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የተሰጠ መሆኑን እና ይህን ቅጽ ከፈረምኩኝ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ልጄ እንዳይመረመር ማድረግ የምችል መሆኑን ተድቻለሁ። ለዚህ ምርመራ ፈቃድ መስጠት ካልፈለግኩኝ፣ ልጄ እንደማይመረመር ተረድቻለሁ። በምርመራ ሂደቱ በማንኛውም ደረጃ ላይ በልጄ ላይ ግምገማ እንዲደረግ መጠየቅ እንደምችል እና ግምገማ እንደሚደረግ እረዳለሁ።

| ☐ ፈቃዴን እሰጣለሁ ☐ ፈቃዴን አልሰጥም<br>የESIT ፕሮግራም ከላይ የተገለጹትን ተግባራት እንዲያከውን ወይም እንዳያከናውን በመረጃ ላይ የተመሰረ ፈቃድ። | |
|---|---|
| **የወላጅ(ጆች) ሥም** | |
| **የወላጅ(ጆች) ፊርማ** | **ቀን** |

| **የተቀበለው ሰው ስም/ማዕረግ/ኤጀንሲ** | **ቀን** |
| --- | --- |
| | |

*አባሪዎች፤ የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናትን የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች [የወላጅ መብት])*
*ማስታወሻ ወላጆች የዚህ ቅጽ ግልባጭ የሚደርሳቸው ሲሆን የተፈረበመት ቅጂ ደግሞ በልጁ የጨቅላነት ጊዜ አገልግሎት ማህደር ውስጥ ይካተታል።*